# ከግብፆች" አንጃ ግራንጃ" በስተጀርባ

ኢዛና ዘመንፈስ 03/21/14

ኢትዮጵያውያን በአባይ ውሃ ከግብፆች ጋር በጥብቅ ተሳስረናል። ይህ ተፈጥሮአዊ ቁርኝት ለሁለቱም ሀገራት ህዝቦች የጋራ ህልውና ትርጉም ያለው ዘላቂ ጥቅም በሚሰጥ ፍትሐዊ መንገድ እንዲቀጥል ማድረግ ካልተቻለ ደግሞ ውጤቱ በጎ አይሆንም። ለተፋሰሱ የውሃ ሀብት ሰማኒያ አምስት ከመቶውን እንደምታዋጣ የሚነገርላት የራስጌ ሀገር ኢትዮጵያን የበይ ተመልካች እንድትሆን የተፈለገበት የ1929 እና የ1959 ዓ/ም ውል እንዲፀና መሻት ደግሞ ጉዳዩን ወደ ለየለት የአንድ ወገን ይዞታነት ለማጠቃለል እንደመሞከር ይቆጠራል።

ይህን ነባራዊ እውነታ አበክሮ የተረዳው የኢትዮጵያ መንግስት የዓባይ ተፋሰስን ሀገራት የሚያቆራኛቸው ጉዳይ የተመሰረተበት የቅኝ ግዛት ዘመን ውል ቅጥ ያጣ ኢ-ፍትሐዊነት ጎልቶ በሚስተዋልበት የአንድ ወገን ፍላጎት ላይ አተኩሮ የተፈረመና ኢትዮጵያ የሌለችበት በተለይም ከአሁኑ ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ጋር ሲነፃፀር ፈፅሞ ያረጀ-ያፈጀ ስለመሆኑ የማስገንዘብ ጥረት ከጀመረ ዓመታት ተቆጥረዋል። ዛሬ "የናይል ተፋሰስ ሀገራት የጋራ ስምምነት ማዕቀፍ" በመባል የሚታወቀውን ለፍትሐዊ የውሃ ክፍፍል ተግባራዊነት አዲስ ምዕራፍ የከፈተ ሰነድ ማርቀቅና መፅደቅ የተቻለውም ኢትዮጵያ ላለፉት በርካታ ዓመታት በጉዳዩ ዙሪያ ተነሳሽነቱን ወስዳ ንቁ የአስተባባሪነት ሚና ስለተጫወተች ነው።

በእርግጥም ደግሞ ከዓለማችን ታላላቅ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች መካከል በርዝመቱ ቀዳመሚ የሆነው ግብፅ የተሰኘችውን ሰሜን አፍሪካዊት ሀገር"የበረሃዋ ገነት" በመባል እንደትታወቅ ያደረጋት የዓባይ ወንዝ ውሃ እትብቱ ለሚቀበርባት ኢትዮጵያ አንዳችም ጥቅም ላይ ሳይውል ቆይቷል። በተፋሰሱ መዳረሻ ላይ ለምትገኘው አገራቸው "ከፈጣሪ የተለገሳት ፀጋ" እንደሆነ አድርገው ለሚቆጥሩት ግብፃውያን ዓባይ የህልውናቸው መሰረት መሆኑ እርግጥ ነው። ወንዙ ለሚመነጭባት የራስጌ ሀገር ኢትዮጵያ ግን ያተረፈላት ነገር ቢኖር ለም አፈሯን እያጋዘ የመሬትቷ ለምነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲያሽቆለቁል ማድረግ ነው።

ስለዚህም የኢ.ፌዴሪ መንግስት የዓባይ ወንዝ ውሃን ለመላው የተፋሰሱ ሀገራት ህዝቦች ዘላቂ ዕጣ - ፈንታ መቃናት ትርጉም ያለው የጋራ ጥቅም እንዲሰጥ ለማድረግ የሚያስችል ፍትሐዊ የስምምነት ማዕቀፍ ማዘጋጀት እንደሚያስፈልግና ጉዳዩ ለነገ የሚባል እንዳልሆነ ጭምር አበክሮ በማስገንዘብ ረገድ የመሪ ተወናይነትን ሚና እንዲጫወት መገደዱ ያለምክንያት አልነበረም።

በዚህ መሰረትም ገና ከደርግ ውድቀት ጀምሮ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ህዝቦች መፃኢ ዕጣ - ፈንታ ከሚወሰንባቸው ሀገራዊ አጀንዳዎች መካከል አንዱና ምናልባትም ዋነኛው ጉዳይ የዓባይ ወንዝ ውሃን ገድበን ለዘላቂ የጋራ ልማት ማዋል ስለመሆኑ ተገቢውን ግንዛቤ የማስጨበጥ እንቅስቃሴ በአንዳንድ የመንግስት ተቋማት ውስጥ ይካሄድ እንደነበረ ማስታወስ ይቻላል።

ይህ ማለት ደግሞ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ኢሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብ በዓባይ ወንዝ ላይ እንደሚገነባ ይፋ እስከተደረገበት መጋቢት24፣ 2003 ዓ/ም ድረስ የኢትዮጵያ መንግስት በጉዳዩ ዙሪያ መሟላት የነበረባቸውን መሰረታዊ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎች ለማሟላት ጥረት ከማድረግ ቦዝኖ አያውቅም። የኤሌትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድቡን የመገንባት ሂደት በይፋ ከተጀመረ በኋላ ባሉት ሶስት ዓመታት ውስጥ የተስተዋለው ተግባራዊ እንቅስቃሴ የሚያረጋግጥልን እውነትም ሀገራችን ይህን ግዙፍ ፕሮጀክት ለማከናወን ስትነሳ በበቂ ጥናት ላይ የተመሰረተ ዕቅድ መንደፏንና አስፈላጊውን ቅድመ-ዝግጅት ማደረጓን ነው።

ከዚህ አጠቃላይ ግንዛቤ አኳያ የግንባታ ሒደቱ የተጀመረውን ስድስት ሺህ ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ሃይል የሚያመነጭ ግድብ በታቀደለት ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ ሲባል የሚደረገው እርብርብ ለአንድም ቀን እንኳን ዝንፍ ያለበት አጋጣሚ ካአልነበረም። ይህን በፍትሐዊ የጋራ ተጠቃሚነት መርህ ላይ የተመሰረተ ፅኑ አቋም ግልፅነት በተሞላበት መልኩ እያራመደች የምትገኘው ኢትዮጵያ፣ ጉዳዩን ያየዘችበት የሰከነና ተገቢ ጥንቃቄ ያልተለየው ሁኔታ በዓለም አቀፉ የዲፕሎማሲ ማህበረሰብ ዘንድ አድናቆት እየተቸረው ስለመሆኑም መረጃዎች ያመለክታሉ።

ለምሳሌ ሰሞኑን (መጋቢት 4 ቀን 2006 ዓ/ም) ካርቱም ውስጥ በተካሄደ "የምስራቅ ናይል ሀገራት የምክክር መድረክ" ላይ አዘጋጆቹ ኢትዮጵያና ሱዳን በህዳሴው ግድብ የግንባታ ሒደት ዙሪያ ያላቸውን ተመሳሳይ አቋም ከመቸውም ጊዜ በተሻለ የባለሙያዎች ማብራሪያ አስደግፈው ማቅረብ በመቻላቸው ምክንያት፣ የምክረ ሃሳብ ሒደቱን ለመታዘብ በስፍራው ከታደሙ የበርካታ ሀገራት አምባሳደሮች ዲፕሎማሲያዊ ከበሬታን አግኝተዋል። ቀደም ሲል የዚሁ "የምስራቅ ናይል ሀገራት የምክክር መድረክ" የተሰኘው ተከታታይ ውይይት አባል የነበረችው ግብፅ በአንፃሩ፣ መድረኩን ጥላ እንደወጣችና ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ የምትገነባውን የህዳሴ ግድብ ለማስቆም ያለመ ዓለም አቀፋዊ ድጋፍ ለማሰባሰብ ፊቷን ወደ ምዕራባውያኑ ሃያላን መንግስታት እንዳዞረች አይዘነጋም።

ኢትዮጵያና ሱዳን ታላቁ የሕዳሴ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብ በዓባይ ወንዝ ላይ ስለተገነባ የታችኞቹን የተፋሰሱ ሀገራት ህልውና ሊፈታተን የሚችል አሳሳቢ ችግር ሊፈጠር ቀርቶ፣ ከቶንውም ግድቡ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን በጎ ውጤት እንደሚያመጣ የጋራ ግንዛቤ ከመጨበጣቸው የተነሳ፣ ይህንኑ የትብብር መንፈስ ይበልጥ እያጎለበቱት መቀጠላቸው የሚያስመሰግናቸውን ያህል፣ ግብፆች ግን አሁንም ድረስ "አንጃ ግራንጃቸውን" ለማስተጋባት ከመሞከር እንዳልቦዘኑ ነው መረጃዎች የሚጠቁሙት። በዚህ ረገድ ከግብፅ በኩል የሚስተዋለውን አጠቃላይ እውነታ የሚከታተሉ አንዳንድ ወገኖች እንደሚሉት፣ ግብፃውያኑ ስለጉዳዩ ምን ዓይነት አቋም እንዳላቸው እንኳን በለየለት መልኩ መግለፅ የቻሉበት አጋጣሚ እስከ ዛሬ ድረስ አለመታየቱ በእርግጥም ሰዎቹ "አንጃ-ግራንጃ" ላይ መጠመዳቸውን ያመለክታል።

ይህ ሁኔታ "የግብፆች አንጃ - ግራንጃ ለምን አስፈለገ?" የሚል ጥያቄ እንድናነሳ የግድ ይላል። ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብ መገንባት ከጀመረ አንስቶ ይፋዊ የመነጋገሪያ አጀንዳ የመሆን ዕድል ያገኘበት ታሪካዊ አጋጣሚ ተፈጥሯልና ማንኛውም ጉዳዩ ይመለከተኛል የሚል ወገን ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ ሒደቱን በጥሞና መከታተል እንደሚጠበቅበት አያጠያይቅም።

እንደዚህ ዓይነቱን የበርካታ ሀገራትን ህዝቦች ዘላቂ እጣ ፈንታ እስከ ወዲያኛው ያቆራኘና ነባራዊውን እውነታ አምኖ ከመቀበል በሚመነጭ የጋራ መግባባት ወይም ስምምነት ላይ ተመስርቶ የሚወሰን ፍትሐዊ ውሳኔን የሚጠይቅ ቁልፍ ጉዳይ በተመለከተ የሚደረግ

ውይይት የተለየ ትኩረት ሊስብ እንደሚችልም መገመት አያዳግትም፡፡ ይሁን እንጂ አሁን ኢትዮጵያና ሱዳን ብቻ ግንኙነታቸውን ከመልካም ጉርብትና በላይ ወደ ሆነ የወንድማማችነት ደረጃ ለማሳደግ እየተጠቀሙበት ካሉት የምስራቅ ናይል ሀገራት የምክክር መድረክ ግብጽ ራሷን ያገለለችበት ምክንያት አሳማኝ አይደለም ማለት ይቻላል፡፡

ከዚህ አጠቃላይ የግል ምልከታዬ ተነስቼ ግብጽ እንደ ሀገር ከታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብ ግንባታ አኳያ የምታንፀባርቀውን አቋም ስገመግመው ስለጉዳዩ የተሟላ ግንዛቤ ካለመጨበጥ የሚመነጭ፤ ወይም ደግሞ እውነታውን በተሳሳተ መልኩ የመረዳት ችግር ያለባቸው ሆኖ ይሰማኛል፡፡ ብዙውን ጊዜ በዚሁ ወቅታዊ ጉዳይ ዙሪያ የመንግሥት ባለስለጣናትን ጨምሮ አንዳንድ  ግብፃውያን ምሁራንና ታዋቂ ፖለቲከኞቻቸው የሚሰነዝሩት አስተያየት እርስ በርስ የሚጣረስ ነው ቢባልም ተገቢ ይመስለኛል፡፡

ይህ የሆነበት መሰታዊ ምክንያት ግብፃውያኑ ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ ስለምትገነባው እጅግ በጣም ግዙፍ የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብ ጉዳይ እንደ ሀገር የለየለት አቋም ሳይዙ በመቆየታቸው ሊሆን እንደሚችል መገመት አይከብድም፡፡ ግብፆች በዚህ ረገድ አቋማቸውን ግልጽ አድርገው ማስቀመጥ እየቻሉ ለምንድነው ይህን ያህል ጊዜ በአጉል ማቅማማትና አንጃ ግራንጃ ያባከኑት?  የሚል ጥያቄ የሚያነሱ ወገኖች ጥቂት እንዳልሆኑም ይገባኛል፡፡ ስለዚህ እኔ በበኩሌ ለዚህ  ጥያቄ ምላሽ ይሆናል የምለውን ሃሳብ ሰጥቼ ጽሁፌን ወደማጠቃለል አመራለሁ፡፡

አንዳንድ ታዛቢዎች እንደሚሉት ከሆነ ግብፃውያኑ ምናልባትም በኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች "ሳይሸወዱ" እንዳልቀሩ የሚያመለክቱ እውነታዎችን ይጠቅሳሉ፡፡ እንደነዚህ ወገኖች አስተያየት ሀገራችን በዓባይ ወንዝ ላይ ስድስት ሺህ ሜጋዋት የኤሌክትሪክ ሃይል የሚያመነጭ የህዳሴ ግድብ ልትገነባ ቆርጣ ስለመነሳቷ መንግስት በይፋ ከገለፀበት መጋቢት 2003 ዓ/ም ጀምሮ አንዳንድ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ዜናው  "የኢ.ህ.አ.ዲ.ግ መንግሥት የውስጥ ችግሩን የሚያረግብለት መስሎት ያቀነባበረው የፖለቲካ ድራማ ነው"  የሚል ማስተባበያቸውን በስፋት ሲያናፍሱ መስተዋላቸው ግብፆችን ሳያሳምን አልቀረም ብዬ እገምታለሁ፡፡

ታዛቢዎቹ ወገኖች ለዚህ ግምታቸው መነሻ የሆናቸውን ምክንያት ሲያስረዱም “አንዳንድ የግብጽ መንግስት ባለስልጣናት ዛሬም ድረስ የግድቡ ግንባታ ሰላሳ ከመቶው ተጠናቋል የሚባለው ለውስጥ ፖለቲካ ትርፍ ማግኛ ነው እንጂ ገና ምኑም አልተነካ” በሚል የሚያቀርቡትን መከራከሪያ ይጠቅሳሉ። በተለይ የሆስኒሙባረክን ከስልጣን መውረድ ተከትሎ በግብጽ ፖለቲካ ውስጥ የበላይነትን የመያዝ አጋጣሚ ያገኘው የሙስሊም ወንድማማቾች ፓርቲ የመንግስትነት ስልጣን ጨብጦ በቆየባቸው ወራት ከአንዳንድ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች ጋር የጠበቀ ግንኙነት መፍጠር ለዚህ አስርጂነት ይጠቅሳሉ።

በእርግጥም ደግሞ ይህ አስተያየት ከተራ መላምት የመነጨ አለመሆኑን የሚያመለክቱ እውነታዎችን በዋቢነት ማንሳት ይቻላል፡፡ ወጣም ወረደ ግን ግብፆች በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብ ግንባታ ዙሪያ ተገቢውን ግንዛቤ ለመጨበጥ የሚያስችላቸውን ትኩረት ሰጥተው ክትትል እንዳያደርጉና በጊዜ ቁርጥ ያለ ወይም የለየለት አቋማቸውን ከማሳወቅ ይልቅ መያዣ መጨበጫ በሌለው አንጃ ግራንጃ እንዲጠመዱ ከማድረግ አኳያ የኛ አገር ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች መንግስትን ለማጥላላት ሲሉ ይፋዊ ባልሆነ መልኩ የሚያናፍሱት ውዠንብር አሉታዊ አስተዋጽኦ አይኖረውም ማለት ይከብዳል፡፡

ምክንያቱም በዚህ ረገድ የሚካሄደው ኢህአዲግ መራሹን መንግስት ተአማኒነት ለማሳጣት ያለመ የማጥላላት ዘመቻ ስፋትና ጥልቀቱ የሚናቅ እንዳልሆነ ከነባራዊው እውነታ መረዳት አያዳግትምና ነው፡፡ ለአብነት ያህልም ባሳለፍነው 2005 ዓ/ም ላይ በተለይ እዚህ መዲናችን አዲስ አበባ ውስጥ በእስልምና ሃይማኖት ሽፋን የተቧደኑ አክራሪ ሙስሊሞችና ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከሕገ መንግስታዊ ስርዓቱ ባፈነገጠ የአመጽ መንፈስ ሀገራዊ ገጽታችንን ጥላሼት ለመቀባት ያለመ እንቅስቃሴያቸውን ለተከታታይ ሳምንታት ያለማ፟ረጥ ማካሔዳቸው አይዘነጋም፡፡ ከዚያን ጊዜው ፖለቲካን ከሃይማኖት ጋር የማጋባት ሙከራ በስተጀርባ የግብጽ “ሙስሊም ብራዘር ሁድ” የሚያስተባብረው ፀረ ኢትዮጵያ ሴራ እንደነበረም ይታመናል፡፡

እናም በቅርቡ “ኢህአዲግ መራሹ መንግስት በሰሜን አፍሪካ ሀገራት የታየውን መሬት አንቀጥቅጥ የህዝብ ቁጣ ከመፍራቱ የተነሳ በደመነፍስ (ያለምንም ጥናት) ዓባይን ለመገደብ መወሰኑ ከግብጽ በኩል የጦርነት መዘዝ ማስከተሉ እንደማይቀር ሲረዳ የአልበሽርን ድጋፍ

ፍሊጋ ከኢትዮጵያ የድንበር መሬት ላይ ቆርሶ ለሱዳን እንደሰጠ ደርሰንበታል"  የሚል መሰረተ ቢስ ወሬ ፈጥረው በተለመደ የዲያስፖራ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች ጭፍን ጥላቻ እያቀነባበሩ ወደ አገር ውስጥ ያዛመቱትም ከግብፆች አንጃ ግራንጃ በስተጀርባ የሚዶልቱና የህዳሴው ግድብ ግንባታ ጉዳይ የእግር እሳት የሆነባቸው ጽንፈኛ የተቃውሞው ጐራ ፖለቲከኞች ስለመሆናቸው ጥርጥር አይኖረውም፡፡

ምክንያቱም እነዚህ ጨለምተኝነት የተጠናወታቸው ሃይሎች ገና ከመነሻው የተቃውàቸው ማጠንጠኛ አድርገው የያዙት ጉዳይ ኢህአዴግ መራሹን መንግስት አመኔታ ለማሳጣት ያለመ የማጥላላት ዘመቻ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ፣ "የሀገራችን መንስት ዓባይን እገድባለሁ ሲል እውነት መስሏችሁ ነገሩን ከቁብ እንዳትጥፉት "  በሚል ከራሳቸው የቁም ቅዠት የመነጨ ባዶ መላ ምት ግብጻዊያኑን ጭምር ወደ አላስፈላጊ የስሌት ስህተት ሊያስገቧቸው እንደሚችሉ መገመት ከእውነታው መራቅ አይሆንም፡፡

እናም ኢትዮጵያ በአባይ ወንዝ ላይ የምትገነባውን የሕዳሴ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብ በተመለከተ ከግብጽ በኩል የሚስተዋለው ጉዳዩን እንደ አዲስ አጀንዳ እያነሱ ለማወሳሰብ የመሞከር አዝማሚያና አላስፈላጊ አንጃ ግራንጃ፣ መቋጫ እንዳይገኝለት በማድረግ ረገድ ምናልባትም የኛ አገር ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች አፍራሽ አስተዋጽኦ ሳይታከልበት አንደማይቀር  በገመት ተገቢ ነው፡፡

በተረፈ ግን የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የሚከተለው የውጭ ፖሊሲ የሀገራትን የጋራ ጥቅም መሰረት ያደረገና በማንኛውም ሉዓላዊ ሀገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባትን ፈጽሞ የማይቀበል እንደሆነ እንኳንስ ኢትዮጵያውያን ግብጾችም ያውቁታል ተብሎ ይገመታል፡፡ ይህ ነባራዊ ሀቅ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ እኛ ኢትዮጵያዊያን እጅ ለእጅ ተያይዘን በምናካሂደው ፈረጀ ብዙ የፀረ ድህነት ትግል የዐባይ ወንዝ ውሃን ገድበን የሀራዊ ሕዳሴያችን መገለጫ የሆነውን የኤሌክትሪክ ሃይል ለማመንጨት ስንነሳ ከመቼውም ጊዜ በላይ ፍትሀዊነትን ያማከለ የጋራ ተጠቃሚነትን መሰረት ላደረገ መርህ መገዛት እንደሚኖርብን አበክረን መገንዘባችንን እነሆ ተግባራችን ይመሰክራል፡፡

ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ጭምር ልክ እንደ ሱዳን ነባራዊውን እውነታ በፀጋ መቀበል ሲገባቸው አሁንም ድረስ በአላስፈላጊ አንጃ ግራንጃ መጠመድን የመረጡ ከሚመስሉት ግብጻዊያን ፖለቲከኞች በስተጀርባ ማንም ኖረ ማን፣ ኢትዮጵያ ታላቁን የሕዳሴ

ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብ በታቀደለት ጊዜ ውስጥ ገንብታ ከማጠናቀቅ ሊያግዳት አይችልም፡፡ ምክንያቱም የግድቡን ግንባታ የተጀመረው  የማንንም እርዳታ ወይንም ድጋፍና እገዛ በመተማመን ሳይሆን እኛ ኢትዮጵያዊያን  በራሳችን አቅም ብቻ መስራት እንደምንችል ለዓለም እናሳያለን ከሚል ቁጭት በመነጨ ሀገራዊ ቃል ኪዳን ነውና፡፡